ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ Since 1991

# መለዕክተ ኢሰመጉ

አንደኛ አመት ቁጥር አምስት መጋቢት 2012 ዓ/ም

የኮሮና ቫይረስ በኢትዮጵያ የመንግስት እርምጃዎችና አሁናዊ የህዝብ የጥንቃቄ ሁኔታዎች

‘ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው”

# < <ቅድሚያ ለሰብዓዊነት! > >



# ርእሰ አንቀጽ

ኢሰመጉ

# ቅድሚያ ለሰብዓዊነት!

ዓለምን ያዳረሰው የኮሮና ቫይረስ በኢትዮጵያም በመከሰቱ በመንግሥትና በግለ ሰብ ደረጃ የተለያዩ የመከላከል ርምጃዎች እየተወሰዱ ናቸው፡ ፡ የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል ወረርሽኝ ሲከሰት ፈጣን ርምጃ መውሰድ ከየትኛውም ወገን የሚጠበቅ ቢሆንም በአገራችን ከሰብዓዊነት መንፈስ የራቁ ድርጊቶች ሲፈጸሙ አስተውለናል፡፡ በዚህ ጊዜ የሕዝብን ደኅንነት የመጠበቅ ትልቁን ኃላፊነት የተሸከመው መንግሥት እንደመሆኑ በፌደራልም ሆነ በክልል መንግሥታት የሚወሰዱ የመከላከል ርምጃዎች ዜጎችን በሽታው ሊያስከትል ከሚችለው በላይ ለከፋ ችግር የሚዳርጉ መሆን እንደሌለባቸው እናምናለን፡፡ ምንም እንኳ የክልልና የፌደራል መንግሥታት እንዲህ ባለው ወቅት የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ እስከማወጅ የሚደርስ ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣን ቢኖራቸውም በብዙዎቹ የክልል መስተዳድሮች የተወሰዱት ርምጃዎች ድንገተኛና ከፌደራል መንግሥት እንዲሁም ከሌሎች የክልል መስተዳደሮች ውሳኔዎችና ርምጃዎች ጋር ያልተናበቡ በመሆናቸው ዜጎችን ለከፋ ችግር ዳርገዋል፡፡ ክልሎች ለዜጎች የመሰናዶ ጊዜ ሳይሰጡ ካሳለፏቸው ድንገተኛ ውሳኔዎች የተነሣ በብዙ አካባቢዎች የከተማና የአገር አቋራጭ የሕዝብ ማመለስና የሆቴል አገልግሎቶች በመቋረጣቸው በተለያዩ ምክንያቶች ከቋሚ የመኖሪያ አድራሻቸው ርቀው የሚገኙ በርካታ ሰዎች ተጉላልተዋል፡፡ ትምህርት በመስጠት ሊታለፉ የሚችሉ ጥፋቶችን «ፈጽመዋል» በተባሉ ዜጎች ላይ በመንግሥት የጸጥታ አካላት በተወሰደ ከልክ ያለፈ የኃይል ርምጃ የሰው ሕይወት ጠፍቷል፤ አካል ጎድሏል፡፡ እንዲህ ዓይነት ድንጋጤ ወለድ ድርጊቶች የሚፈጸሙት የመንግሥት አካላት ምን ጊዜም ቢሆን ተግባራቸውን ሲወጡ ቅድሚያ ለሰብዓዊነት እንዲሰጡ የሚያስገድድ ሥልጡን ባሕል ባለማዳበራችን ነው፡፡ ስለሆነም፣ ወደ ፊት የቫይረሱ ሥርጭት እየተስፋፋ በሄደ ቁጥር የከፋ ጉዳት እንዳይደርስ «የሕዝብን ደኅንነት» ለመጠበቅ ታሳቢ ተደርገው የሚወሰዱ ርምጃዎች ጥንቃቄን የተላበሱ ሊሆኑ እንደሚገባ እናሳስባለን፡፡ በዚህ ፈታኝ ወቅት የታዘብነው ሌላው ጉዳይ በማኅበረሰባችን ውስጥ ያለው የእርስ በርስ መጨካከን ነው፡፡ የቫይረሱን ሥርጭት ለመግታት ያግዛሉ በተባሉ የሕክምና ቁሳቁስ ላይ ብቻ ሳይሆን በመሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች ላይ በጥቂት ቀናት ልዩነት የተፈጠረው እጅግ የተጋነነ የዋጋ ንረት በማኅበረሰብ ደረጃ ወደ የት እያሽቆለቆልን እንደሆነ

ቆም ብለን እንድናስብ የሚያስገድድ ነው፡፡ ወረርሽኙ እንዳይከሰት፤ ቢከሰት እንኳ በአጭር ጊዜ ውስጥ በቁጥጥር ሥር እንዲውል ለማድረግ በግለ ሰብ ደረጃ ምን እያደረግን እንደሆነም ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባል፡፡ በሕክምና ባለሙያዎች የሚሰጡ ምክሮችን አለመከተል፣ ለበሽታው የሚያጋልጡ ድርጊቶችን የሚፈጽሙትን ከስኅተታቸው ለመመለስ የሚሞክሩ ሰዎችን እንደ ጥፋተኛ ቆጥሮ ማሸማቀቅና መደብደብ ሊወገዝ ይገባዋል፡፡ በሽታው የሚተላለፍበት መንገድ ከሰዎች መስተጋብር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው በመሆኑ በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ፍርሐት ተፈጥሮ ሕሙማንና ቤተሰቦቻቸው ለማኅበራዊ መገለል እንዳይዳረጉ የግል ሕይወታቸው፤ ግላዊነታቸው እንዳይደፈር መጠንቀቅ ይገባል፡፡ ስለሆነም፣ የኮሮና ቫይረስ ሥርጭትን ለመከላከል በመንግሥት፣ በማኅበረሰብና በግለ ሰብ ደረጃ የጥንቃቄ  ርምጃዎች ሲወዱ ቅድሚያ ለሰብዓዊነት በመስጠት እንዲሆን እናሳስባለን፡፡


ተግባራቸውን ሲወጡ ቅድሚያ ለሰብዓዊነት እንዲሰጡ የሚያስገድድ ሥልጡን ባሕል ባለማዳበራችን ነው፡፡ ስለሆነም፣ ወደ ፊት የቫይረሱ ሥርጭት እየተስፋፋ በሄደ ቁጥር የከፋ ጉዳት እንዳይደርስ «የሕዝብን ደኅንነት» ለመጠበቅ ታሳቢ ተደርገው የሚወሰዱ ርምጃዎች ጥንቃቄን የተላበሱ ሊሆኑ እንደሚገባ እናሳስባለን፡፡

በዚህ ፈታኝ ወቅት የታዘብነው ሌላው ጉዳይ በማኅበረሰባችን ውስጥ ያለው የእርስ በርስ መጨካከን ነው፡፡ የቫይረሱን ሥርጭት ለመግታት ያግዛሉ በተባሉ የሕክምና ቁሳቁስ ላይ ብቻ ሳይሆን በመሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች ላይ በጥቂት ቀናት ልዩነት የተፈጠረው እጅግ የተጋነነ የዋጋ ንረት በማኅበረሰብ ደረጃ ወደ የት እያሽቆለቆልን እንደሆነ ቆም ብለን እንድናስብ የሚያስገድድ ነው፡፡

ወረርሽኙ እንዳይከሰት፤ ቢከሰት እንኳ በአጭር ጊዜ ውስጥ በቁጥጥር ሥር እንዲውል ለማድረግ በግለ ሰብ ደረጃ ምን እያደረግን እንደሆነም ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባል፡፡ በሕክምና ባለሙያዎች የሚሰጡ ምክሮችን አለመከተል፣ ለበሽታው የሚያጋልጡ ድርጊቶችን የሚፈጽሙትን ከስኅተታቸው ለመመለስ የሚሞክሩ ሰዎችን እንደ ጥፋተኛ ቆጥሮ ማሸማቀቅና መደብደብ ሊወገዝ ይገባዋል፡፡

በሽታው የሚተላለፍበት መንገድ ከሰዎች መስተጋብር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው በመሆኑ በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ፍርሐት ተፈጥሮ ሕሙማንና ቤተሰቦቻቸው ለማኅበራዊ መገለል እንዳይዳረጉ የግል ሕይወታቸው፤ ግላዊነታቸው እንዳይደፈር መጠንቀቅ ይገባል፡፡

ስለሆነም፣ የኮሮና ቫይረስ ሥርጭትን ለመከላከል በመንግሥት፣ በማኅበረሰብና በግለ ሰብ ደረጃ የጥንቃቄ ርምጃዎች ሲወዱ ቅድሚያ ለሰብዓዊነት በመስጠት እንዲሆን እናሳስባለን፡፡ሊያስከትሉ የሚችሉ አደገኛ ጥሪዎችን ከማስተላለፍ እንዲታቀቡ በዚህኛው ዕትም እናሳስባለን፡፡



## መልእክተ ኢሰመጉ

አሳታሚ
የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ

### የዝግጅት ክፍሉ ባልደረቦች

ብንያም አባተ
ዳን ይርጋ
ሱራፍኤል ግርማ
ጥበቡ ኃይሉ
ገላውዲዮስ ግሩም

### የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ
ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7
የቤት ቁጥር= 112/37
ስልክ ቁጥር =0118685706
ፖ.ሳ.ቁ =2432
ኢሜል= info@ehrco.org

ሁሉም መብቶች ለሁሉም!

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ)

ኢሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን (FIDH) አባል፣ የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት (OMCT) አባልና የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ሕብረት (DefendDefenders) መሥራች አባልም ነው፡፡

# ሰዋዊ

# የኮሮና ቫይረስ ሥርጭትን ለመከላከል እየተወሰዱ ያሉ ርምጃዎች ከሰብዓዊ መብቶች አንጻር ሲፈተሹ

በሱራፍኤል ግርማ

እ.ኤ.አ ማርች 11 ቀን 2020 የዓለም የጤና ድርጅት በቫይረስ የሚተላለፈው COVID-19 በሽታ ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ መሆኑን ዐውጆ የቫይረሱን ሥርጭት ለመግታት መንግሥታት አስቸኳይና  መጠነ ሰፊ ርምጃዎች እንዲወስዱ አሳስቧል፡፡

የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባሕላዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን ማንኛውም ሰው ሊደረስበት በሚቻልከፍተኛ የአካልና የአእምሮ ጤንነት የመኖር መብት ያለው መሆኑን፣ የቃል ኪዳኑ ተዋዋይ አገራትም ወረርሽኝን ለመከላከል፣ ለማከምና ለመቆጣጠር የሚቻልበትን ሁኔታ የመፍጠር ግዴታ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡

የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የሕግ መሠረት ኖሯቸው የሚወሰዱ ርምጃዎች በተወሰኑ መብቶች ላይ ገደብ ሊጥሉ መቻላቸው ተቀባይነት ቢኖረውም ተፈጻሚነታቸው አንድ ወጥ የሆነ፣ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሚቆይ፣ ሰብዓዊ ክብርን የማይጋፋ፣ በየጊዜው የሚገመገምና ለማሳካት ከታለመው ዓላማ ጋር ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባል፡፡

በአሁኑ ሰዓት ዓለምን አስጨንቆ ያለውን ዓይነት በሽታ ለመቆጣጠር መንግሥታት በሚወስዷቸው ርምጃዎች ሰለባ ከሚሆኑ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መካከል ሐሳብን በነጻ የመግለጽ፣ መረጃ የመሰብሰብና የማሠራጨት መብት አንዱ ነው፡፡ መንግሥታት በማኅበረሰብ ውስጥ የሚፈጠሩ የጤና ችግሮችን በተመለከተ ለሕዝብ ትምህርታዊ መረጃ በአስቸኳይ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ቢሆንም የኮሮና ቫይረስ ሥርጭት በተከሰተባቸው የመጀመሪያዎቹ ሳምንታት ያስተዋልነው እውነታ ከዚህ ፍጹም ተቃራኒ ነበር፡፡

በሽታው በተከሰተባት ቻይና ስለ አዲሱ ቫይረስ በበይነ መረብ መረጃ ያሠራጨው ሐኪም ሊ ዌንሊያን  ‹‹አሉባልታ በማሠራጨት›› ተከስሶ የፖሊስ ምርመራ ተካሂዶበታል፡፡ በሥራው ምክንያት እርሱም ራሱ ለበሽታው ተጋላጭ ስለነበር ቅጣት በሚመስል ሁኔታ በቂ የሕክምና ክትትል ሳያገኝ ሕይወቱ አልፏል፡፡

በሽታውን ‹‹የዴሞክራቶች ማወናበጃ››፣ ‹‹የቻይና ቫይረስ›› በማለት ሲያቃልሉ የከረሙት የአሜሪካው ፕሬዚደንት ዶናልድ ትራምፕ ወረርሽኙ ሊክዱት በማይችሉት ደረጃ በአገራቸው ከተሠራጨ በኋላም ቢሆን መንግሥታቸው እየወሰደ ስላለው ርምጃ እንደ ‹ሲ ኤን ኤን› ካሉ የብዙኃን መገናኛ ተቋማት ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ከመስጠት ይልቅ ‹‹አስቀያሚ ጥያቄ . . .›› በማለት ማጣጣልን መርጠዋል፡፡

እነዚህን የሌሎች አገራት ተሞክሮዎችን በምሳሌነት ያነሣነው ለሕዝብ ጠቃሚ መረጃ የሚያሠራጩ የጤና ባለሙያዎችንና ጋዜጠኞችን ማሸማቀቅ አለፍ ሲልም መቅጣት ወረርሽኙን አስመልክቶ ውጤታማ የመልዕክት ልውውጥ እንዳይኖር በማድረግ ሕዝብ መንግሥት በሚወስዳቸው የመከላከል ርምጃዎች ላይ ዕምነት እንዳይኖረው እንደሚያደርግ ለማሳሰብ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ከቫይረሱ ሥርጭት ጋር በተገናኘ እስካሁን ያለው የትምህርታዊ መረጃ ሥርጭት መልካም ቢሆንም የዓለም የጤና ድርጅት ባሳሰበው መሠረት በሽታው በአፍሪካ በወረርሽኝ መልክ ሲከሰት በመንግሥት ላይ ከሚፈጥረው ገመና ገላጭ ዘርፈ ብዙ ተጽእኖ የተነሣ የሥርጭት አድማሱንና የጉዳት መጠኑን መደበቅ አማራጭ ሆኖ እንዳይወሰድ ያሠጋል፡፡

በአገራችን ያለውን ነባራዊ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የማኅበረሰቡን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚያስቆም የአስቸኳይ ጊዜ ርምጃ እንደማይወሰድ በፌደራል መንግሥት ደረጃ ቢገለጽም የክልል መንግሥታት በተናጠል የሚወስዷቸው ርምጃዎች ድንገተኛ መሆናቸውንና የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ እስከማወጅ የደረሱ መሆናቸውን ተመልክተናል፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች ከቋሚ አድራሻቸው ርቀው የሚገኙ ዜጎች የክልል መንግሥታት በወሰዷቸው ድንገተኛ ርምጃዎች ከባድ መጉላላት ደርሶባቸዋል፡፡ የፌደራልም ይሁን የክልል መንግሥታት አስገዳጅ የሆኑ የእንቅስቃሴ ዕቀባ ርምጃዎችን ሲወስዱ ዜጎች ለሕልውናቸው መሠረታዊ የሆኑትን ምግብ፣ መጠለያና የሕክምና አገልግሎት የማግኘት ሰብዓዊ መብቶች መነፈግ እንደሌለባቸው ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ መሆን አለበት፡፡

ከዚህ በተጨማሪ፣ አገሪቱ ከኮሮና ወረርሽኝ ሥጋት ነጻ እስክትሆን ድረስ ብዙዎቹ

# ሰዋዊ

የጤና ተቋማት ድንገተኛ አደጋ ከሚደርስባቸው ሰዎች በቀር የ COVID-19 ሕሙማንን ብቻ እንደሚያስተናግዱ አስታውቀዋል፡፡

ምንም እንኳ በሽታው በደንብ የተደራጀ የጤና ሥርዓት ያላቸው ሀብታም ሐገራትን እንኳ ሳይቀር በጣም የፈተነ ከመሆኑ አኳያ ያለንን ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብት ሁሉ በማስተባበር ወረርሽኙን በመከላከል ተግባር ላይ እንዲውል መታቀዱ የሚያስነቀፍ ባይሆንም ውሳኔው ሰዎች ሲታመሙ የሕክምና አገልግሎትና እንክብካቤ የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባው ነበር፡፡

በድንጋጤ፤ ድንገት በሚተላለፉ ውሳኔዎች ዜጎችን ከአንድ በሽታ ተከላክሎ በሌላ ሕመም እንዲሞቱ ላለመፍረድ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ወቅት ከማንም በላይ ለበሽታው ተጋላጭ የሚሆኑት የሕክምና ባለሙያዎች ናቸው፡፡

ዐቅምበሚፈቅደው ልክ ከአደጋ ነጻ በሆነና በጤናማ ሁኔታ ውስጥ ሥራቸውን የማከናወን መብታቸው ካልተከበረ ውጤቱ የከፋ ስለሚሆን አስፈላጊው የመከላከያ ግብዐት ተሟልቶላቸውየሚሠማሩ መሆናቸውን መንግሥት ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

በሌሎች አገራት የበሽታ ወረርሽኝ ሲቀሰቀስ «የጤና ባለሙያዎችና የሆስፒታል ሠራተኞች በሽታ ያስተላልፋሉ» በሚል ምክንያት ለጥቃት ተጋላጭ ሲሆኑ በመስተዋሉ በኢትዮጵያም (በተለይም በገጠር) ይህ ችግር እንዳይከሰት በብዙኃን መገናኛ አማካይነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ለሕዝቡ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

አለማወቅ የሚያስከትለው ጥቃት ሰለባ የሚሆኑት የሕክምና ባለሙያዎች ብቻ አይደሉም፡፡

ከዚህ በፊት የጤና ቀውሶች በወረርሽኝ መልክ በተከሰቱ ጊዜ ሕሙማንና ቤተሰቦቻቸው የአድልዎና መገለል ሰለባዎች መሆናቸው አይዘነጋም፡፡

በኢትዮጵያ ቁጥራቸው የበዛ የኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሕሙማን የሚደርስባቸውን ማኅበራዊ መገለል በመፍራት ተገቢውን ሕክምና ሳያገኙማለፋቸው የሚታወስ ነው፡፡

በምዕራብ አፍሪካም በኢቦላ ቫይረስ ታምመው የዳኑ ሰዎች ከመኖሪያ ቀዬአቸው ተፈናቅለዋል፣ ከሥራ ተባርረዋል፣ በቤተሰቦቻቸው ተገፍተዋል፣ አካላዊ ጥቃት ተፈጽሞባቸዋል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ከተከሰተበት ጊዜ አንሥቶ ኢትዮጵያን ጨምሮ በተለያዩ አገራት የውጭ አገር ዜጎችን የማግለልና የጥቃት ዒላማ የማድረግ አደገኛ አዝማሚያዎች ተስተውለዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በቫይረሱ የሚያዙ ዜጎች ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ በማኅበረሰቡ ውስጥ ከሚፈጠረው የተጋላጭነት ሥጋት የተነሣ በሕሙማን፣ ታክመው በዳኑ ሰዎች፣ በቤተሰቦቻቸውና በቅርብ ወዳጆቻቸው ላይ የማግለልና የአድልዎ ድርጊት እንዳይፈጸም አስቀድሞ የመከላከል እንቅስቃሴ መጀመር የዘመቻው አንድ አካል መሆን አለበት፡፡

በመጨረሻም፣ የዓለም የጤና ድርጅት እንደሚመክረው የኮሮና ቫይረስ ሥርጭትን ለመግታት በግለ ሰብ ደረጃ ሊወሰድ የሚችለው ትልቁ የጥንቃቄ ርምጃ እጅን በሳሙናና በውኃ መታጠብ ነው፡፡ ነገር ግን በኢትዮጵያ የገጠር መንደሮች ቀርቶ በዋና ከተማዋ አዲስ አበባ የንጹሕ ውኃ አቅርቦት በዝቀተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡

ይህም ብቻ ሳይሆን እንደ ሳሙና፣ አልኮሆል፣ ‹ሳኒታይዘር› ያሉ የፋብሪካ ምርቶች የሆኑ የንጽሕና መጠበቂያ ሸቀጦች እጥረት መከሰቱና ዋጋቸውም ማሻቀቡ ዜጎች ቀላል የመከላከያ መንገዶችን እንዳይጠቀሙ እንቅፋት መፍጠሩ አይቀርም፡፡ ስለሆነም፣ መንግሥት ወረርሽኙን ለመከላከል አስፈላጊ የሆኑትን የንጽሕና መጠበቂያ ምርቶችንና የንጹሕ ውኃ አቅርቦትን እውን በማድረግ የዜጎችን ንጹሕና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት የሚከበርበትን ሁኔታ ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡

(ይህ ጽሑፍ ‹ሒዩመን ራይትስ ዎች› እ.ኤ.አ ማርች 19 ቀን 2020 Human Rights Dimensions of

COVID-19 Response በሚል አርእስት ይፋ ባደረገው ሠነድ ላይ በመመሥረት የተዘጋጀ ነው)

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

# የኮሮና ቫይረስ በኢትዮጵያ

# የመንግስት እርምጃዎችና አሁናዊ የህዝብ የጥንቃቄ ሁኔታዎች

ዳን ይርጋ



## መግቢያ

የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ለመጀመሪያ ጊዜ ከተቀሰቀሰበት ከቻይናዋ ውሀን ከተማ በመነሳት በከፍተኛ ፍጥነትና ስፋት እየተዛመተ አሁን በዓለም ላይ ቫይረሱ ያልደረሰበት ሀገር የለም ለማለት የሚያስቸግር ደረጃ ላይ ደርሰናል፡፡

ይህ ቫይረስ ምንም አይነት የዘር፣ የእድሜ፣ የፆታ፣ የሀይማኖት፣ የኢኮኖሚ ሁኔታ ሳያግደው ሁሉንም የሰው ዘር በስፋትና በፍጥነት እያጠቃ ያለና በወረርሽኝነት ደረጃ ላይ የሚገኝ ገዳይ በሽታ ነው ፡፡

## ቫይረሱ ወደ ኢትዮጵያ የገባበት ሁኔታ

የኮሮና ቫይረስ ወደ ኢትዮጵያ በአንድ ጃፓናዊ ዜግነት ባለው ሰው ገባ ከተባለበት ጊዜ ማለትም ከመጋቢት 3 2012 ዓ.ም ጀምሮ ከፍተኛ መደናገጥ ፈጥሯል ይህም የተለያዩ መገለጫዎች አሉት በተለይም የንግድ እንቅስቃሴው ላይ የተለያዩ መገልገያ ቁሳቁሶችና ሸቀጣሸቀጦች ላይ ያላግባብ የዋጋ ጭማሪ፣ ምርቶችን መደበቅና ማከማቸት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በስፋት ተከስቷል፡፡

መንግስት ይህንን ኢኮኖሚያዊ ምክንያት የሌለውን እና አላስፈላጊ የሆነ የዋጋ ንረትና ህገ ወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎች ለመቆጣጠር ህገ ወጥ ነጋዴዎች ላይ ህጋዊ እርምጃዎችን ከመውሰድ አንስቶ የገቢያውን እንቅስቃሴ ለማረጋጋት የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል አሁንም የተለያዩ ስራዎችን በመስራት የገቢያው እቅስቃሴ ለማረጋጋት እየሞከረ ይገኛል፡፡

## የቫይረሱ ስርጭትን ለመከላከል እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች

መንግስት የቫይረሱን ስርጭት ለመቆጣጠር የተለያዩ የትምህርት ተቋማትን በመዝጋትና በርካታ ሰዎች የሚሳተፉበትን ስብሰባዎች ከመከልከል በተጨማሪ ስለኮሮና ቫይረስ የግንዛቤ መስጫ ስራዎችን በተለያየ መንገድ በመስጠት ላይ ይገኛል ለምሳሌ በሬድዮ፣ በቴሊቪዥን፣ በበራሪ ፅሁፎች፣ በአደባባይ በመለፈፍ፣ በአጭር የፅሁፍ መልዕክቶች እንዲሁም የማህበራዊ ሚዲያዎችንን በመጠቀም ህዝብን ለማስተማር እየሞከረ ይገኛል፡፡

መጀመሪያ ላይ የኮሮና ቫይረስን ለመከላከል ለህዝብ የሚሰጡ የነበሩ ትምህርቶች በርካታ ክፍተቶች ነበሩበት ለምሳሌ:

- የአካል ጉዳተኞችን በተለይም መስማት ለተሳናቸው ሰዎች በሚገባቸው የምልክት ቋንቋ ትምህርቱ እየተሰጠ አልነበረም፣
- በሀገሪቱ በስፋት በሚነገሩባቸው የተለያዩ ቋንቋዎች ትምህርቱና የግንዛቤ ማስጨበጫው አልተሰጠም ነበር፣
- የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህት አተኩረው ሲሰጡ የነበረው በአዲስ አበባና ትንሽ ከፍ ያለ እንደሆነም በዋና ዋና የክልል ከተሞች ውስጥ ብቻ ያተኮረ ነበር፣
- በአሁኑ ወቅት እየተሰጡ ያሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶች መሻሻል እያሳዩ ቢሆንም አሁንም በርካታ ማስተካከያ ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ በተለይም የሚሰጡት ትምህርቶች ወጥነት ባለውና እርስ በርስ በመቃረን ህዝብን የሚያሳስቱ እንዳይሆኑ መንግስትና የሚመለከተቻው አካላት ሁሉ የበኩላቸውን ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

## ህዝብ የተዘናጋባቸው ሁኔታዎች

የኮሮና ቫይረስ ከቻይና አልፎም የዓለም ስጋት በሆነበት ወቅት በሀገራችን ያለው የግንዛቤና የጥንቃቄ ሁኔታዎች እጅግ በጣም ያነሰ ነበር ይህም ብቻ ሳይሆን ቫይረሱን አሳንሶ ማየትና ወደኛም አይመጣም የሚል የተሳሳቱ ግንዛቤዎች ጭምር ይታዩ ነበር፡፡

በአጠቃላይ በአሁኑ ሁኔታ የሀገሪቱ በኮሮና ቫይረስ የመጠቃቷ ጉዳይ እውነት ከመሆኑም አልፎ የተጠቂዎች ቁጥር ከሀምሳ በላይ ሆኗል የሁለት ሰዎችም ህይወት በዚሁ ቫይረስ ምክንያት አልፏል፡፡

## አሁን የቫይረሱ ስርጭት ያለበት ሁኔታ

የቫይረሱ ስርጭት በስፋት የምርመራ ስራ ባለመጀሩ አሁን ያለው በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር ትንሽ ሊመስል ይችላል ይሁንና የምርመራ ስራው በስፋት መሰራት ሲጀምር ቁጥሩ በዚሁ ልክ ይጨምራል የሚል ግምት አለ፡፡

ይህ ፅሁፍ እስከተዘጋጀበት ወቅት ድረስ በሀገሪቱ እስከ ዛሬ ድረስ 65 ሰዎች በቫይረሱ የተጠቁ መሆኑን መንግስት የገለፀ ሲሆን ሁለት ሰዎችም ህይወታቸውን አጥተዋል፡፡

## በሀገሪቱ በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች:

- በአዲስ አበባ - 48
- በድሬዳዋ - 2
- በአዳማ - 3
- በባህር ዳር - 1
- አዲስ ቅዳም- 2

በድምሩ 65 ምንጭ የጤና ሚኒስቴር

## ምክረ ሀሳቦች

- ቫይረሱን ለመከላከል የሚሰሩ ስራዎች የሰዎችን መብቶች በተባባስ መልኩ በማይጥሱ መልኩ መሆን አለባቸው ይልቁንም ዜጎች የመከላከል ስራዎችን አምነውበት እንዲሰሩና እንዲሳተፉ እንዲሁም የበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ በሚያበረታታ መልኩ ቢሆን የተሻለ ውጤት ስለሚያመጣ መንግስት በዚህ ረገድ ቢያስብበት ፣
- ቫይረሱን ለመከላከል የሚሰሩ ማናቸውም አይነት ስራዎች የአካል ጉዳተኞችን ልዩ ፍላጎቶች ባማከለ መልኩ መሰራት አለበት፣
- መጠለያ የሌላቸውን ዜጎች ማለትም የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን፣ የጎዳና ተዳዳሪዎችን ሁኔታም መንግስት አቅም በፈቀደ መልኩ ድጋፍና እርዳታ ማቅረብ አለበት፣
- የቫይረስ መመርመሪያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶችን አቅም በፈቀደ መጠን በሁሉም ክልሎች ጭምር በማሟላት ምርመራውን በስፋት በማካሄድ የቫይረሱ ስርጭት በሀገራችን ያለውን ስፋት ለማወቅ ስለሚያስችን ይህንን ስራ በፍጥነት ቢሰራ ስርጭቱን ለመቆጣጠር ያግዛል፣
- በክልሎች ውስጥ የሚደረጉ የቅድመ መከላከል ስራዎች፣ የማስተማር ስራዎች፣ የምርመራ ስራዎች የለይቶ ማቆያ ስራዎችና ሌሎችም እንቅስቃሴዎች በተቀናጀ መልኩ መሆን አለባቸው
- የለይቶ ማቆያዎችን በተቻለ መጠን ከህዝብ ጋር በመወያየት መሰረታዊ ግብዓቶች በተሟሉበት ሁኔታ ማረጋጀት፣
- የተለያዩ የገበያ ስፍራዎች፣ በትራንስፖርት መያዛ ቦታዎች፣ በመዝናኛ ስፍራዎችና በተለያዩ ስፍራዎች አሁንም የህዝብ መዘናጋት በስፋት ይታያል ስለሆነም መንግስትና የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በዚህ ጉዳይ ላይ የማስተካከያ ስራ መስራት ይገባቸዋል፡፡

## ማጠቃለያ

በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 41 ንዑስ አንቀፅ 4 መሰረት መንግስት የዜጎችን የጤና አጠባበቅና የማህበራዊ ሁኔታዎችን በተመለከተ በየጊዜው እየተሻሻለና እየጨመረ የሚሄድ ስራዎችን መስራት እንዳለበት በግልፅ ደንግጓል ስለሆነም የመንግስትን ግዴታ በዚህ አንቀፅ ለመረዳት ይቻላል፡፡

መንግስት የዜጎችን ጤና የመጠበቅ ከተለያዩ የወረርሽኝ በሽታዎችም የመከላከልና የመጠበቅ ግዴታ ተጥሎበታል ይሁንና ዜጎችም የራሳቸውን ግዴታ መወጣጥ ይጠበቅባቸዋል በተለይም መንግስት በየጊዜው የሚያወጣቸውን የተለያዩ መመሪያዎችን በማክበርና በመተግበር የድርሻቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ለመከላከል ሁላችንም የድርሻችንን እንወጣ፡፡

ቸር ያሰማን!

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

________የዓለም የጤና ድርጅት ወረርሽንነቱን ያወጀበት www.who.int/emergencies/diseases/novel-coronavirus-2019/enents-a

http://www.moh.gov.et/ejcc/ Ministry of Heath-Ethiopia

የኢሰመጉ ጋዜጣዊ መግለጫ መጋቢት 17 2012 ዓ.ም.

ኬላ

ሕግ

# የፌደራል እና የክልል መንግስታት እንደምን ሰነበቱ!?

ጥበቡ ኃ.

ዓለም በዚህ ሰዓት ኮሮና የተሰኘ አስጨናቂ ደዌ ክፉኛ ወጥሯታል፡፡ ከመነሻው የአንዲት ሩቅ ምስራቃዊት ሐገር እዳ ተደርጎ የነበረው #COVID-19 አሁን ለማናችንም የማይመለስ መቅሰፍት መሆኑን አሳይቶናል፡፡ የዓለም ጤና ድርጅት በሽታው ዓለም ከፊቱ የተጋረጠበት ሁነኛ ጠላት የሆነ ወረርሺኝ መሆኑን ማወጁን ተከትሎ ሁሉም ቀልቡን መጣል ጀምሯል፡፡ አሁን በዓለም-አቀፍ ደረጃ የተጠቂው ቁጥር ሚሊዮን ተሻግሯል፤ ሟቾችም መቶ ሺህ ሊደርሱ ነው፡፡

ኮሮና ወደ ሐገራችን መግባቱን መንግስት በይፋ ካረጋገጠበት መጋቢት 4/2012 ዓ.ም ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ከትንሸዋ ጎረቤታችን ጅቡቲ እንኳን በቁጥር ላነሱ ሰዎች በተደረገው ምርመራ 60 የተሻገሩ ሰዎች በቫይረሱ መያዛቸው የተረጋገጠ ቢሆንም ቁጥሩ ብዙዎችን ጭንቀት ውስጥ ከቷል፡፡ የቫይረሱን ስርጭት ለመከላከል የፌደራል እና የክልል መንግስታት የሰዎች እንቅስቃሴን ከመገደብ አንስቶ አስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅን የመሳሰሉ እርምጃዎችን እየወሰዱ ነው፡፡ እርምጃዎቹ ግን የተጠና እና የተናበበ ስላለመሆኑ ብዙ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ፌደራል መንግስት አስቀድሞ ዋነኛ ትኩረቱን ለክፉ ቀን በሚል በሚደረገው የገቢ ማሰባሰብ እና የአቅም ግንባታ ስራዎች ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ ጎን ለጎን የሰራተኞች ቅነሳ፣ የከተማ ትራንስፖርት ስርጭት፣ የትምህርት እና የማረሚያ ተቋማትን በተመለከተ ይበጃሉ ያላቸውን ውሳኔዎች በመስጠት ለበሽታው ስርጭት ምላሽ ለመጠት ሞክሯል፡፡ ከሰሞኑ ደግሞ የመከላከል እርምጃዎቹን የበለጠ ለማጠንከር እና በተለመደው የአደጋ መከላከል አሰራር ምላሽ መስጠት የሚቻል ባለመሆኑ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 93 (1) (ሀ) መሠረት ለአምስት ወራት የሚቆይ የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ ደንግጓል፡፡

የክልል መንግስታት በበኩላቸው በተናጠል ይበጀናል ያሉትን በማድረግ ላይ ተጠምደዋል፡፡ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል ያልተለመደ የነበረው የክልል መንግስታት አስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ በትግራይ ክልል በኩል ታውጇል፡፡ አማራ ክልል ወደ ክልሉ የየብስ የሕዝብ ማመላለሻዎች እንዳይገቡብኝ ሲል በተመረጡ ከተማ አስተዳደሮች ደግሞ ከትራንስፖርት አገልግሎት መቋረጥ እስከ ዘግቶ መቀመጥ የሚደርሱ ውሳኔዎችን አሳልፏል፡፡ በደቡብ እና በቤንሻንጉል ክልል አብዛኛው ትኩረቱን የትራንስፖርት አገልግሎቱ ላይ ያደረጉ ክልከላዎች ተላልፏል፡፡ ኦሮሚያ ሕዝቡ ሊተግብራቸው ይገባሉ ያላቸውን 12 ትዕዛዛት ይፋ አድርጓል፡፡ ድሬዳዋ፣ ሐረሪ፣ ጋምቤላ እና የሶማሌ ክልልም ድንግርግሩ የወጣ ውሳኔ ማሳለፋቸውን ይፋ አድርገዋል፡፡

ነገር ግን የፌደራሉም ሆነ የክልል መንግስታቱ ውሳኔ መናበብ የጎደለው እና ድንግርግር የበዛበት ነበር፡፡ አስቀድሞ የቫይረሱ መገኘት ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት የመጀመሪያዎቹ 14 ቀናት ውስጥ የቫይረሱን ስርጭት የሚያሳየው የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት ይፋ ሳይደረግ በፊት የክልል መንግስታቱ በተለይ የወሰዱዓቸው እርምጃዎች የዜጎችን ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ መብት የገደበ ነበር፡፡ ከዚህም አልፎ የአየር ትራንስፖርት እንዲገባ ተፈቅዶ የየብስ ትራንስፖርት ግን የተከለከለበት አመክንዮ በቂ እንዳልነበር ለመረዳት ቀላል ነው፡፡ በመሰረቱ የዜጎች ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ ነጻነት ሊገደብ የሚችልበት ምክንያት መኖሩ እርግጥ ቢሆንም ክልከላው ግን የዜጎችን የኢኮኖሚ አቅም መነሻ በማድረግ አግባብ ያልሆነ ልዩነት እንዲኖር ማድረግ የለበትም፡፡

በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 32 ሥር የተቀመጠው የዜጎች የመዘዋወር መብት ድንገተኛ ገደብ የተጣለበት በመሆኑ የዜጎች ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ወድቋል፡፡ ከዚህ አንጻር ካየነው የክልል መንግስታት ውሳኔ የበሽታውን የስርጭት መጠን ያላገናዘበ እና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ አሳልፈዋል ለማለት ይከብዳል፡፡ በእርግጥ አሁን የበሽታው ስርጭትም እየሰፋ በመምጣቱ ከዚህም የባሱ ክልከላዎች እና ገደቦች መጣላቸው አይቀርም፡፡ የፌደራሉ መንግስትም በሁሉም ክልሎች ተፈጻሚ የሚሆን የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ የደነገገ በመሆኑ እና የበሽታውን ስርጭት እና የችግሮቹን ስፋት መሠረት ያደረጉ ክልከላዎች እና ገደቦች በአብዛኛዎቹ መብቶች እና ነጻነቶች ላይ ይጣላሉ፡፡

የሆነው ሆኖ እንደዚህ ባሉ አስቸጋሪ ጊዜዎች ወቅት ከመንግስት እና ከጤና ባለሙያዎች የሚሰጡትን መመሪያ እና ትዕዛዝ በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ እና ችግሩን በአጭር ጊዜ በቁጥጥር ሥር ለማዋል ትብብር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በመንግስት በኩልም የሚወጡት መመሪያዎች እና ትዕዛዞች በተለየ መልኩ የተጋረጠብንን አደጋ ለመከላከል የሚያስችሉ እንዲሆኑ ወቅታዊ መረጃዎችን እና ሙያዊ እውቀትን መሠረት ያደረጉ መሆን እንደሚገባቸው ማሳሰብ ተገቢ ነው፡፡

ቸር ያሰማን!

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

# ቀለም




## “ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው”

ገካውዴዮስ ግሩም

የኮረና ተህዋሲ ከ መጀመሪያው የቻይናዋ ህዋን ከተማ አንድ ብሎ ተነስቶ አፍታም ሳይቆይ በመቶ ቀናት ውስጥ  ዓለም ላይ 1.8 ሚሊዮን ሰዎች በበሽታው ያጠቃ ሲሆን የሞቱትም ከ 110 ሽህ ተሻግረዋል።

በ አህጉራችን አፍሪካም ከ 52 ሀገራት በላይ በሽታው ተዳርሷል ከነዚህም ውስጥ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከ 3 ሳምንታት በፊት ገደማ የመጀመሪያውን በ ተውህሲው የተያዘ ሰው ይፋ አድርጋ አሁን ከ 70 ተሻግራ 3 ሰዎችንም በዚህ ጦሰኛ በሽታ ምክኛት ቀብራለች። ይሁን እና በዚህ ወቅት ሌላኛው ፈተና ሆኖ እየተጠቀሰ ያለው የሀሰት መረጃ ነው። አያቶቻችን ሲተርቱ “ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው” እንዲሉ አለማችን በጭንቀት በተወጠረችበት በዚህ ክፉ ጊዜ ከወረርሽኙ እኩል የሚነዛው የሐሰት መረጃ እና ወሬ አለምን እያሸበረ ይገኛል። ከማሸበርም ባለፈ በነዚህ በሐሰት በሚዛመቱ መረጃዎች ምክንያት የ አለም የጤና ድርጅትም ሆነ የህክምና ባለሙያዎች የሚሰጧችው ትክክለኛ መረጃዎች እሚተገብራቸው ጠፍቶ ሰዎች ወደከፋ ጉዳት እየገቡ ይገኛሉ።

የነዚህ የሐሰት መረጃዎች ምንጭ በትክክል ምን እንደሆነ መረዳት ቢያዳግትም በቅንነት ለጉዳዩ ክብደት ለመስጠት ከማሰብ ጀምሮ ሆን ብሎ ሰውን ለማሸበር እና ለግል ጥቅም ታስቦ ሊደረግ ይችላል።

ይሁን እንጂ በተለያዩ ማህበራዊ ድረ ገጾች እሚሰራጩት ሐሰተኛ መረጃዎች በጊዜ መፍትሄ ካልሰጠናቸው ፈተና እንደሚሆኑብን ጥርጥር የለውም

እሄንንም በተመለከተ መረጃዎች ትክክል መሆናቸውን ለማረጋገጥ እና ካልሆኑም መውሰድ ስላሉብን እርምጃዎች ባለሙያዎች እሚሉትን ላካፍላችሁ ወደድኩ መልካም ቆይታ።

ኮሮናቫይረስ: ሐሰተኛ መረጃ እንዳይስፋፋ ምን ልናደርግ እንችላለን?

ከኮሮናቫይረስ ጋር በተያያዘ ሐሰተኛ መረጃዎች በይነ መረብን እያጥለቀለቁት ይገኛሉ። ባለሙያዎች ደግሞ ኅብረተሰቡ “መረጃ ማጥራትን” እንዲለማመድ ጥሪ አቅርበዋል። አሳሳች መረጃ እንዳይስፋፋ ምን ማድረግ ይችላሉ?

1. ቆም ብለው ያስቡ

ቤተሰቦችዎን እና ጓደኞችዎን መርዳት ይፈልጋሉ። አዲስ ምክር ባገኙ ቁጥር በኢሜይል፣ በዋትስአፕ ፣ በፌስቡክ ወይም በትዊተር በፍጥነት ሊያካፍሏቸው ይችላሉ ነገርግን እንደባለሙያዎች ከሆነ የተሳሳተ መረጃን ለማቆም ማድረግ የሚችሉት አንድ ቀላል ነገር ቆም ብሎ ማሰብ ነው። ስለመረጃው ጥርጣሬ ካለዎት ለአፍታ ቆም ብለው በደንብ ይመልከቱት።

2. ምንጭዎን ያረጋግጡ

መረጃውን ከማስተላለፍዎት በፊት መረጃው ከየት እንደመጣ ይጠይቁ። ምንጩ “የጓደኛ ጓደኛ” ወይም “የአክስቴ ባልደረባ ጎረቤት” ከሆነ መረጃው ትልቅ ጥያቄ ምልክት ውስጥ ይገባል ማለት ነው። በቅርቡ ከአንድ “ሁለተኛ ዲግሪ ካለው አጎቴ” የሚል አንድ አሳሳች መረጃ በፍጥነት የተዛመተበትን መንገድ ለመመልከት ችለናል በዚህ መረጃ ላይ ያሉት የተወሰኑት ጉዳዮች ትክክለኛ ነበሩ። ለምሳሌ የኮሮናቫይረስ ስርጭትን ለመግታት እጅ መታጠብን ያበረታታል።ሌሎቹ ነገሮች ግን ጎጂ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ያልተረጋገጡና በሽታውን ለመመርመር የሚረዱ ናቸው የተባሉ ዝርዝሮች ቀርበውበታል።

“አስተማማኝ የመረጃ ምንጮች እንደ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የዓለም ጤና ድርጅት ወይም እንደ በሽታ መቆጣጠሪያ ማዕከል ያሉ የሕዝብ ጤና ተቋማት ናቸው” ሲሉ መቀመጫውን በእንግሊዝ ያደረገውና የመረጃዎችን ትክክለኛነት የሚያረጋግጠው ‘ፉል ፋክት’ የተባለው ድርጅት ምክትል አርታኢ ክሌይር ሚልን ያስረዳሉ።

3. ሐሰተኛ ሊሆን ይችላል?

አቀራረቡ አሳሳች ሊሆን ይችላል የመንግሥትን ጨምሮ ኦፊሴላዊ አካውንቶችን፣ ድረ ገጾች እና ባለሥልጣኖችን ገጽ ማስመሰል ይቻላል። ፎቶ በማንሳት መረጃው ከታመነ አካል የመጣ እንዲመስልም ሊደረግ ይችላል።

የታወቁ እና የተረጋገጡ አካውንቶችና ድረ ገጾችን ይጎብኙ። መረጃውን በቀላሉ ማግኘት ካልቻሉ ምናልባት ሐሰተኛ ሊሆን ይችላል። ጽሑፉ፣ ቪዲዮው ወይም ገጹ አጠራጣሪ ምናልባትም ሐሰተኛ ይሆናል።

ካፒታል ሌተርስ (Capital letters) እና ወጥያልሆኑ የፊደላት ቀርጾች (fonts) አጠቃቀም መረጃዎችን ትክክለኛነት በሚያረጋግጡ ባለሙያዎች መረጃው አሳሳች ሊሆን እንደሚችል እንደአመላካች ከሚጠቀሙባቸው ነጥቦች አንዱ መሆኑን የፉል ፋክት ምክትል አርታኢ ክሌይር ሚልን ይገልጻሉ።

4. እውነት ስለመሆኑ እርግጠኛ አይደሉም? ስለዚህ መረጃውን አያጋሩ

እውነት “ሊሆን ይችላል” በሚል ብቻ መረጃዎችን አያስተላልፉ። በዚህ ምክንያት መልካም ከማድረግ ይልቅ ጉዳት እያደረሱ ይሆናል። ብዙ ጊዜ መረጃዎችን የምንለጥፈው እንደሐኪሞች ወይም የህክምና ባለሙያዎች ያሉ ባለሙያዎች ባሉባቸው ቦታ ከሆነ ይህ ጥሩ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ስለጥርጣሬዎ ግልፅ መሆንዎን ያረጋግጡ። ያጋሩት ፎቶ ወይም ጽሑፍ ከአውዱ ውጭ ሊወሰድ ስለሚችልም ይጠንቀቁ።

5. እያንዳንዱን እውነታ በተናጥል ይፈትሹ

ዋትስአፕ ላይ እየተሰራጨ ያለ የድምፅ ማስታወሻ አለ። በማስታወሻው ውስጥ የምትናገረው ግለሰብ ሆስፒታል ውስጥ የሚሠራ “ጓደኛ ካለው ባልደረባ” ያገኘቻቸውን ምክሮች እየተረጎመች ስለመሆኑ ትናገራለች ሆኖም ትክክለኛ እና ትክክል ያልሆኑ ምክሮች የተደባለቀቡት ነበር። በጣም ጠቃሚ የሆኑ ምክሮችን ዝርዝር በሚያገኙበት ወቅት በመሃል በሚያገኙት አንድ ትክክለኛ ምክር (ለምሳሌ እጅ መታጠብ ጠቃሚ ስለመሆኑ በመገለጹ) ብቻ ሁሉንም ትክክል ነው ብሎ ማመን ቀላል ነው ግን ሁሌም እንደዚያ አይደለም፤ ይጠንቀቁ!

6. ከስሜታዊ መረጃዎች ይጠንቀቁ

እንደእውነቱ ከሆነ ፍርሃት፣ ቁጣ፣ ጭንቀት ወይም ደስታ የሚፈጥሩብን ስሜታዊ ነገሮች ናቸው በብዛት የሚሰራጩት።

“ፍርሃት ሐሰተኛ መረጃዎች በበፍጥነት እንዲዛመቱ ከሚያደርጉ ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ ነው” ሲሉ ጋዜጠኞች በበይነ መረብ ሐሰተኛ መረጃዎችን እንዲከላከሉ የሚያግዘው ‘ፈርስት ድራፍት’ የተባለው ድርጅት ባልደረባ የሆኑት ክሌይር ዋርድል ይገልጻሉ። ድርጊትን የሚያበረታቱ አስቸኳይ ጥሪዎች ጭንቀትን ለማነቃቃት የተቀየሱ በመሆናቸው ይጠንቀቁ።

“ሰዎች የሚወዷቸው ሰዎች ደኅንነት የተጠበቀ እንዲሆን ለመርዳት ይፈልጋሉ” ስለዚህ ‘ቫይረሱን ለመከላከል የሚረዱ ምክሮች’ ወይም ‘ይህን የጤና ተጨማሪ ምግብ ይውሰዱ’ የሚሉ መረጃዎችን ሲመለከቱ፤ “የሚወዷቸውን ሰዎች ለመርዳት የተቻላቸውን ሁሉ ለማድረግ ይፈልጋሉ “ትላለች ክሌር።

7. ስለአንድ ጉዳይ ያለንን ወገንተኝነት አንዘንጋ

የሆነ ነገር የሚያጋሩት እውነት እንደሆነ ስላወቁ ነው ወይስ በጉዳዩ ስለተስማሙ?

በማኅበራዊ መገናኛ መድረኮች ዙሪያ ጥናት የሚሰራ ማዕከል የምርምር ዳይሬክተር የሆኑት ካርል ሚለር እንደሚሉት በአብዛኛውን ጊዜ የምናጋራቸው መረጃዎች ያለንን እምነታችንን የሚያጠናክሩትን ነው።

“በንዴት ጭንቅላታችንን በምንወዘውዝበት ወቅት ነው በጣም ተጋላጭ የምንሆነው። በዚህ ወቅት ነው ከምንም ነገር በላይ በይነመረብ ላይ የምንሠራውን በሙሉ ማዘግየት ያለብን” ሲሉ ይመክሩናል።

ይህ ጸሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።